# የንግድ ማህበራት ውል አፈፃፀም ችግሮች እና የዳኝነት ሂደት

**ጥናቱን ያከናወኑ ባለሙያዎች፡-**

የትናየት ደሳለኝ

1. የንግድ ውሎችን ለማስፈጸም በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የንግድ ማህበራት ተከራካሪ የሆኑባቸው ፋይሎች ከ1998-2002 ባሉት አምስት አመታት ቁጥራቸው እየጨመረ መምጣቱን ለማየት ተችሏል፡፡
2. በ2002 ተከፍተው እልባት ያገኙት ፋይሎች ከ1988 ዓ.ም እልባት ካገኙት ጋር ሲነፃፀር ቁጥራቸው ከፍ ተኛ ነው፡፡ ይህ እንዳለ ቢሆንም ፍርድ ቤቱ የተከፈቱ ፋይሎችን እልባት የሚሰጥበት ሁኔታ (disposal rate) ከ1998-2002 ዓ.ም ባሉት አመታት ውስጥ በ30% ዝቅ ያለ ነው፡፡
3. በ2001 እና በ2002 ከቀረቡት 131 መዝገቦች መካከል የኮንስትራክሽን፣ የቼክ እና የባንክ ክርክሮች በቁጥር ቀዳሚውን ስፍራ መያዛቸው ታይቷል፡፡
4. እነዚህ ማህበራት ተከራካሪ የሆኑባቸው ክርክሮችን እልባት ለመስጠት 12.5 ወራት መስዷል፡፡ ይህም ከዚህ በፊት በሌሎች አካላት ከቀረቡት ሪፖርቶች ጋር ሲነፃፀር ከፍተኛ ልዩነት መኖሩን ያሳያል፡፡
5. ከቀረቡት ክርክሮች መሃል 70% የሚሆኑት የሚያሸንፉት ሲሆኑ የተቀሩት ደግሞ ውድቅ ይሆኑና በሌሎች ህጋዊ ምክንያቶች ውሳኔ ሳያገኙ የተዘጉ እና በእርቅና በግልግል ዳኝነት የተዘጉ ናቸው፡፡
6. በፌ/ከ/ፍ/ቤት ለክርክር የሚወጣው ወጪን (litigation cost) ስንመለከት የዳኝነት ወጪዎችን የሚከፍሉት በዳኝነት ታሪፍ ማስከበሪያ ደንብ መሠረት ሲሆን ለዳኝነት የሚከፈለውም ክፍያ ከአጠቃላይ የክርክር ገንዘብ መጠን ጋር ሲነፃፀር 1.37% ነው፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታም ለጠበቃ የሚወጣው ወጪ እንደየክርክሩ አይነትና የገንዘብ መጠን ሲለያይ የሚከፈለውም ክፍያ በአማካይ ከሚቀርበው የገንዘብ መጠን ጋር ሲነፃፀር 5.1% ብቻ መሆኑን ያሳያል፡፡
7. የፌዴራል ፍርድ አፈፃፀም መምሪያ በዋናነት የሚፈፅመው ተግባር ከፍርድ ቤቶች የሚሰጡ የፍርድ አፈፃፀም ትዕዛዞችን የሚያስፈፅምና በዚህም የቴክኒክ አገልግሎት ሥራዎችን ማከናወን ሲሆን ትዕዛዞቹን የሚሰጡ ችሎቶች ቁጥር ማነስ፣ የውሳኔ ጥራታቸውም እዚህ ግባ ማይባልና የግልፅነት ችግር በመኖሩ የአፈፃፀም ሥራው ሠንካላ እንዲሆን አድርጎታልና ጥንቃቄ ቢደረግ፡፡

8. ለፍርድ አፈፃጸም መምሪያ የሚላኩ የአፈፃጸም መዝገቦች ይግባኝ መባላቸውና አለመባላቸው ተጣርተው ባለመምጣታቸው ምክንያት አፈፃፀም መምሪያ ብዙ የቴክኒክ ደረጃዎችን ከሄደ በኋላ መዝገቡ ይግባኝ በመባሉ ምክንያት የዕግድ ትዕዛዝ ይመጣና የአፈፃፀም ሥራው እንዲቆም ይደረጋል፡፡ ስለሆነም የአፈፃፀም ሥራው እንዲጓተት ያደርጋል፡፡ ሌላው የፍርድ አፈፃጸም መምሪያ ላይ ፍርድ ያልተሰጠባቸውን ጉዳዮች በተደራቢነት የቴክኒክ ጉዳይ እንዲያጣራ የሚመጡ ትዕዛዞች የሥራ ጫናን በመፍጠር የፍርድ የአፈፃፀም ሥራ ጥራት ማነስ ይዳርጋሉ፡፡ በአጠቃላይ የፍርድ አፈፃፀም ሥራዎችን ለብቻ የሚያከናውኑ የአፈፃፀም ችሎቶች ለብቻቸው ቢደራጁ መልካም ነው ፡፡
9. የግል የንግድ ድርጅቶች ተከራካሪ በሆኑባቸዉ በግልግል ዳኝነት ከታዩ 33 መዝገቦች ላይ በተደረገዉ ዳሰሳ ከተገኘዉ መረጃ ለመገንዘብ እንደተቻለዉ ክስ ለግልግል ዳኞች ጉባኤ ቀርቦ ዉሳኔ እስከሚያገኝ ድረስ በአማካይ 12.8 ወራት /1 ዓመት ከ24 ቀናት/ ይወስዳል፡፡ በመደበኛዉ ፍ/ቤት የሚታዩ ክሶች የሚወስዱትን ጊዜ ለመቃኘት በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ከተወሰኑ መዝገቦች መረጃ የሚያሳየዉ በአማካይ የሚወስደዉ ጊዜ 12.5 ወራት /1 ዓመት ከ15 ቀናት/ እንደሆነ ነዉ፡፡ ይህም የንግድ ድርጅቶች የሚከራከሩባቸዉ ጉዳዮች እልባት የሚያገኙበት አማካይ ጊዜ በመደበኛዉ ፍ/ቤትም ሆነ በግልግል ዳኝነት ተቀራራቢ ቢሆንም በግልግል ዳኝነት የሚሰጡ ዉሳኔዎች በተወሰኑ ቀናት ከፍ/ቤት እንደሚዘገዩ ያሳያል፡፡
10. ለክርክር ከሚወጡ ወጪዎች መካከል በዋናነት የሚጠቀሱት ለዳኝነት የሚከፈል ክፍያ/አበል እና የጠበቃ አበል ናቸዉ፡፡ በተዳሰሱት መዝገቦች በተገኘዉ መረጃ መሰረት በግልግል ዳኝነት ለዳኞች የሚከፈል አበል በአማካይ 6.3% ያህል ሲሆን በመደበኛዉ ፍ/ቤት ደግሞ በአማካይ 1.37 እንደሆነ በተደረገዉ ዳሰሳ ታዉቋል፡፡ የጠበቃ አበልን በተመለከተ በግልግል ዳኝነት የወጪና ኪሳራ ጥያቄ ሲወሰን በአማካይ 5.5% ያህል የሚከፈል ሲሆን በመደበኛዉ ፍ/ቤት ደግሞ የሚወሰነዉ በአማካይ 5.15%

እንደሆነ ማየት ይቻላል፡፡ በአማካይ ከተገኘዉ መረጃ እንደሚታየዉ በግልግል ዳኝነት ለዳኞች የሚከፈል አበል በመደበኛዉ ፍ/ቤት ከሚከፈለዉ ክፍያ በ5.1% ያህል ልዩነት ከማሳየቱ በተጨማሪ በግልግል ዳኝነት ተከሳሽ የዳኝነት አበል ክፍያን ከከሳሽ ጋር እኩል እንዲከፍል በመደረጉ ክርክሩ በግልግል ዳኝነት መታየቱ ተከሳሽ ላይ ተጨማሪ ወጪ ያስከትላል፡፡ ከዚህ መገንዘብ የሚቻለዉ ለከሳሽም ሆነ ለተከሳሽ የግልግል ዳኝነት በተለይም ለዳኞች በሚከፈለዉ አበል ምክንያት ከመደበኛዉ ፍ/ቤት ይልቅ ከፍተኛ ወጪን እንደሚያስወጣ ነዉ፡፡

11. በዚህ ጥናት የታየዉ ሌላ ግኝት የሚያሳየዉ በግልግል ዳኝነት ከተሰጡ ዉሳኔዎች በ26 መዝገቦች /79%/ በዉሳኔዉ ቅር በመሰኘት ወደ ፌ/ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ እንደሚጠየቅ ነዉ፡፡ የግልግል ዳኝነት ዉሳኔ በመደበኛዉ ፍ/ቤት ከሚሰጠዉ ዉሳኔ በተለይ የተለየ ሙያዊ ችሎታን በሚጠይቁ ትላልቅ የንግድ ድርጅቶች መካከል በሚካሄዱ ክርክሮች በተሻለ ሁኔታ ተከራካሪ ወገኖችን ያረካል ተብሎ ስለሚታሰብ ይግባኝ የመጠየቅ ሁኔታዉ ከፍተኛ መሆን ይህንን ሃሳብ የሚያፈርስ ይመስላል፡፡
12. በሌላ በኩል በዳሰሳዉ ከ33 መዝገቦች ዉስጥ 50% ያህሉ በአብላጫ ድምፅ የተሰጡ ዉሳኔዎች መሆናቸዉን እንዲሁም ከነዚህ ዉስጥ 62.5% የሚሆኑት በድምፅ የተለዩ ዳኞች የሰጡት የልዩነት ሃሳብ የሸማቸዉን ወገን የሚደግፍ መሆኑን ለማየት ተችሏል፡፡ ይህም ሁኔታ የግልግል ዳኝነትን/አማራጭ የክርክር መፍቻ ስልቶችን እና የዳኞቹን ገለልተኝነት (Impartiality) ጥያቄ ዉስጥ የሚያስገባ ነዉ፡፡